# የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools)

## የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት (Family Life Education)፣ 10ተኛ ክፍል ውስጥ

*ዳግም-ምልከታ ለማድረግ ያለ-መብት:* ወላጆች እና አሳዳጊዎች፤ በትምህርት ቤት ክፍሉ/division የሚሰጠውን፤ በፕሮግራሙ ውስጥ ጥቅም-ላይ የሚውለውን የጽሁፍ እና የድምፅ-እይታ (audio-visual) ትምህርትን ቁሳቁሶችን ጨምሮ፤ የ'Family Life Education Program'ን በድጋሚ-የመመልከት መብት አላቸው። ወላጆች እና አሳዳጊዎች፤ ልጃቸውን ከ'Family Life Education' የትምህርት-አሰጣጥ፣ ከሁሉም ወይም ከተወሰነው-ከዚህ ክፍል እንዲወጡ-ፈቃድ እንዲያገኙ የማድረግ መብት-አላቸው።

*የፕሮግራም ግቦች:* የACPS፣ የ'Family Life Education' ስርዓተ-ትምህርት፤ ሁሉን-አቀፍ የሆነ፣ ቅደም-ተከተል ያለው ከK-10 ፕሮግራም ሆኖ፤ በቤተሰብ አኗኗር እና በማህበረሰ ግንኙነቶች ላይ - ለዕድሜያቸው-ተገቢ በሆነ የትምህርት-አሰጣጥን አካትቶ እንዲቀርብ የተቀረጸ ነው። የትምህርት-አሰጣጡ የተቀረጸው፤ ሊኖር-የሚያስፈልገውን የወላጅ ተሳትፎን ለማበረታታት፣ አዎንታዊ የሆነ የራስ-ጽንሰ-ሃሳቦችን ለማሳደግ እና ከእኩዮቻቸው-ጋር እኩል-ሆኖ ለመታየት ሲባል - የሚመጣባቸው ጫና መቋቋሚያ፣ እና እንደ ተማሪዎቹ የዕድገት ደረጃዎች እና አቅሞች መሠረት - በዘመናዊ አኗኗር ውስጥ የሚገጥማቸውን ጫናዎች የሚቋቋሙበትን መንገዶች ማቅረብ ነው።

*የፕሮግራም ቅደም-ተከተል:* በቨርጅኒያ የትምህርት መምሪያ (Virginia Department of Education) በታዘዘው-መሠረት፣ በACPS ውስጥ፣ የ'Family Life Education' ስርዓተ-ትምህርት፣ ከK-10ኛ ክፍሎች - በሚከተሉትን የጽንሰ-ሃሳብ ይዘቶች ላይ በ'Standards of Learning' ላይ መሠረት አድርጎ የትምህርት-አሰጣጥን ያካትታል:

1. የቤተሰብ አኗኗር እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች፤
2. የቤተሰብ ግንኙነቶች ያላቸው ከፍተኛ-ዋጋ፤
3. የወሲባዊ-እንቅስቃሴዎችን - ወደ ሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ያለው ከፍተኛ ዋጋ፤
4. የመታቀብ ትምህርት፤
5. ለወንዶች፣ ሴቶች፣ ልጆች፣ እና ማህበረሰቦች፤ ጋብቻ ያለውን - ጥቅሞች፣ አስቸጋሪ-ፈታኝ ነገሮች፣ ኃላፊነቶች እና ከፍተኛ-ዋጋ፤
6. የሰው-ልጅ ወሲባዊ-መለያ (Human sexuality)፤
7. የሰው-ልጅ መራባት/መዋለድ (Human reproduction)፤
8. ያልታሰበ እርግዝና በሚፈጠር ጊዜ፤ ለማደጎ-የመስጠትን አዎንታዊ የሆነ አማራጭ - ያለው ጥቅሞች፤
9. በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች፤ መንስዔ፣ መከላከያ፣ እና የሚያመጡት ችግሮች፤
10. የሰውን-ልጅ ከቦታ-ቦታ ያለፈቃድ ዝውውር (human trafficking)ን መከላከል፤
11. የፍቅር-ጓደኝነት ጥሰት (dating violence) - በዚህ ውስጥ መካተት ያለበት፤ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ማንኛውም የወሲብ ክንውን ከማድረጋቸው በፊት ስምምነት መስጠት፣ ጥቃት-ያለባቸውን የግንኙነት ፀባዮችን ማወቅ፣ የወሲብ ጥቃትን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎችን፣ ሊገኙ-የሚችሉትን የማማከር እና ሕጋዊ የመረጃ-ምንጮችን ማወቅ፣ እና፣ የወሲብ-ጥቃት በሚከሰት ጊዜ - ወዲያውኑ የሕክምና ትኩረት እና ምክርን ማግኘት ጠቃሚነትን፣ እንዲሁም የሕግን አስፈላጊነት፤ እንዲያውቁ ማድረግን ያካትታል፤ እና
12. የአዕምሮ ጤና ትምህርት እና ግንዛቤ።

*የስርዓተ-ትምህርት መስመሮች (Strands):* ስርዓተ-ትምህርቱ፤ በሦስት የመለኪያ ርዕሶች (measurement topics) ዙሪያ የተገነባ - ይህም ጭብጥ-ያለው መስመር (thematic strands)፣ እና የሂደት መደበኛዎች - ግንዛቤዎችን ዘላቂ በማድረግ እና መሠረታዊነት ያላቸውን ሂደቶች በፕሮግራሞ መሃከል-ላይ በማድረግ ላይ ትኩረት አድርጎ-የተገነባ ነው።

1. የእርስ-በርስ ግንኙነቶች (Relationships)
2. የየግል የደህንነት-ጥበቃ (Personal Safety)
3. ዋና ጽንሰ-ሐሳቦች (Core Concepts)
4. እራስን-መቆጣጠር (Self-management)

ለእያንዳንዱ ክፍል - ከእነዚህ የመለኪያ ርዕሶች (measurement topics) ጋር ጎን-ለጎን በማድረግ፤ ግቦችን ማስተላለፍ እና የክንውን-ሂደቶችን ይገመግማል።

*ስርዓተ-ትምህርትን ለአንዳፍታ-በምልከታ-ላይ:* በ10ኛ ክፍል የ‘FLE’ የትምህርት አሰጣጡ ወቅት፤ የሚከተሉት ርዕሶች ላይ - ምላሽ-ተሰጥቶባቸዋል።

# የ10ኛ ክፍል - የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት

**<u>ክፍል/Unit 1:</u> የእርስ-በርስ ግንኙነቶች (Relationships)**

በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች - 10 ጤናማ-የሆኑ የግንኙነት (relationship) ምልክቶች እና 10 ጤናማ-ያልሆነ የግንኙነት (relationship) ምልክቶች - ይማራሉ። ጤናማ-ባልሆኑ ግንኙነቶች (relationships)፣ የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት/dating abuse፣ እርዳታ-እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ እና በተሻለ-ሁኔታ ጤናማ-ግንኙነቶች (healthier relationships)ን እንዴት መገንባት-እንደሚችሉ፤ በመወያየት ጊዜ-ያሳልፋሉ።

1. **ትምህርት/Lesson 1፡ የእርስ-በርስ ግንኙነት ምልክቶች (Relationship Signs) - ጤናማ-የሆነ ወይም ጤናማ-ያልሆነ ግንኙነት/relationships ምልክቶችን የሚለዩ-እና ጤናማ-ያልሆነ ግንኙነት (unhealthy relationship) እንዴት ጤናማ-መሆን እንደሚችል - መንገዶቹን ይማራሉ።**
2. **ትምህርት/Lesson 2፡ ጤናማ-ያለሆነ/Unhealthy ከ - ጥቃት-አድራጊ የሆኑ ግንኙነቶች (Abusive Relationships) ጋር ሲነፃፀር** – በጥቃት ዑደት ውስጥ ያሉትን አራት-ሂደቶችን ማወቅ እና በጤናማ ግንኙነት ባህሪያቶች ውስጥ ያሉትን ተሞክሮዎች ማወቅ።
3. **ትምህርት/Lesson 3፡ ገደብ-ማበጀት (Boundaries) & ስምምነት (Consent)** – ከአካላዊ-ንክኪ ጋር በተያያዘ የግል የገደብ-ድንበሮች/boundariesን መለየት እና እነዚህን-ነገሮች፣ በፍቅር ወይም በፆታዊ ግንኙነት ውስጥ ያላቸውን የመግባቢያነት አስፈላጊነት - ይረዳሉ። እንዲሁም-ደግሞ፣ ስምምነት (consent)ን መረዳት፣ እና ቆይቶ-ንዴትን ማሳየት፣ ጠበኛነት፣ እና የሚፈልጉትን-አረጋጋጭነት ያለው ግንኙነት-ዓይነትን ማወቅ-እንዲችሉ ማድረግ።

**'Standards of Learning’:**
10.2, 10.3, 10.4, 10.7

| | | |
|---|---|---|
| | **ክፍል/Unit 2: የየግል የደህንነት-ጥበቃ (Personal Safety)**<br><br>በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች - ስለ በሕገወጥ-መንገድ ሰዎችን ከቦታ-ቦታ ማዘዋወር (human trafficking) ያለውን-ችግር ይማራሉ፤ እና ሁለቱም - በዓለም-ዙርያ ያለ-ችግሮች እና በራሳቸው-ማህበረሰቦች ውስጥም ያለ-ችግር፣ መሆኑን ይገነዘባሉ። እንዲሁም-ደግሞ፣ በሕገወጥ-ሁኔታ ሰዎችን ከቦታ-ወደቦታ የሚያዘዋውሩ-አዘዋዋሪዎች (human traffickers) - ለሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ተጋላጭ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ሁኔታዎችን ለይተው-የሚያውቁ እና ለራሳቸው እና ለሌሎች እንዴት መሚገት እንደሚችሉ ምልከታ-ያደርጋሉ። በመጨረሻም፣ ተማሪዎች - ስለ ሴት ልጅ ግርዛት/መቁረጥ (SB 1159)፣ ጎጂ-የሆኑ አካላዊ እና ስሜታዊ ተፅዕኖዎችን በመማር፣ ተያያዥ የወንጀል-ቅጣቶች እና የተጎጂዎችን መብቶች በተመለከተ ትምህርት ያገኛሉ።<br><br>1. **ትምህርት/Lesson 1: ሴክስቶርሽን/Sextortion –** በሕገወጥ-መንገድ ሰዎችን ከቦታ-ቦታ ማዘዋወር (human trafficking) ከውጪው-ያለውን ምልክቶች ያስረዳል እና እውቅና-ይሰጣል። በሕገወጥ-መንገድ ሰዎችን ከቦታ-ቦታ ማዘዋወር (human trafficking) ላይ ሊደርሱ ከሚችሉ-አደጋዎች፣ እራሳቸውን የሚከላከሉበትን ስልቶችን ማዘጋጀት እና እርዳታ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መለየት እና በሕገወጥ-መንገድ ሰዎችን ከቦታ-ቦታ ማዘዋወር (human trafficking)ን ሪፖርት-ማድረግ።<br>2. **ትምህርት/Lesson 2: ስለFGM/C መማር –** የሴት ልጅ ግርዛት/መቁረጥ (female genital mutilation/cutting) ምንነቱን-መተርጎም እና አንድ-ሰው ስለ 'FGM/C' እርዳታን እና እገዛን የት እና እንዴት ማግኘት እንደሚችል መሰየም። | **'Standards of Learning':**<br>10.4<br><br>**የስቴት ሕግ-አወጣጥ:**<br>HB 215, HB 1020, SB 1159 |
| | **ክፍል/Unit 3: ዋና ጽንሰ-ሐሳቦች (Core Concepts)**<br><br>በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች - የእርግዝና ምልክቶችን፣ አማራጮችን፣ ጤናማ የእርግዝና ሁኔታዎችን፣ የወሊድ ሂደትን እና የወሊድ አማራጮችን ጨምሮ - እርግዝናን በጥልቀት ይመረምራሉ። ስለ ድጋፍ-ሰጪ ወላጅነት እና ቤተሰቦችም ይወያያሉ። በመጨረሻም፤ ከ'Teen Wellness Center' የሚሰጠውን - ስለ እርግዝና እርዳታ አገልግሎቶች - ይማራሉ።<br><br>1. **ትምህርት/Lesson 1: እርግዝና እና ወሊድ/Pregnancy & Birth –** የእርግዝና ምርመራ እንዴት እንደሚሰራ የሚያብራራ እና ለእያንዳንዱ-እርግዝና ያሉትን ሦስት ሕጋዊ አማራጮችን፣ ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል። በእያንዳንዱን-የጽንስ ጊዜ ውስጥ ያለውን - የፅንስ-እድገት ዋና ዋና ክንውኖች (major milestones) ላይ ምልከታ-ያደርጋል።<br>2. **ትምህርት/Lesson 2: እገዛ-ሰጪ ወላጅነት/Supportive Parenting –** የአንድ-ጥሩ ወላጅ ባህሪያትን የሚያብራራ እና ወጣት-ወላጅ፣ እርዳታ-ለማግኘት ለመሄድ የሚችሉበትን የመረጃ-ምንጮች/resources ስማቸውን-ያቀርባል።<br>3. **ትምህርት/Lesson 3: የ'Teen Wellness Center' - የእርግዝና እርዳታ –** የ'Teen Wellness Center' ለእርግዝና እርዳታን እንዴት እንደሚሰጥ ለይቶ-ማወቅ። በ'Teen Wellness Center' የሚሰጠውን - የወሊድ መቆጣጠሪያ እና የ'STD' መከላከያ አማራጮችን - መሰየም። | **'Standards of Learning':**<br>10.5, 10.6, 10.8, 10.9, 10.10, 10.11, 10.12, 10.13, 10.14, 10.15, 10.16, 10.17 |

**<u>ክፍል/Unit 4:</u> እራስን-መቆጣጠር (Self-management)**

በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች - በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ባህሪያቶች ውስጥ መሳተፍን ወይም መቼ-ለማድረግ በመወሰን-ላይ፣ ተጽዕኖ ሊያሳድሩባቸው የሚችሉትን የግፊት-ሁኔታዎች ላይ ትንታኔ ያደርጋሉ። እንዲሁም-ደግሞ፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ ትክክለኛ የወሲብ ትምህርት (sex ed) መረጃን - የሚያቀርቡ የመረጃ-ምንጮች/resources በማግኘት-ላይ ይዳስሳሉ።

1. **ትምህርት/Lesson 1፡ የእኔ ሕይወት፣ የእኔ ውሳኔዎች/My Life, My Decisions –** በሕይወታቸው ውስጥ፣ ከተለያዩ ሰዎች ስለ ወሲባዊነት/sexuality የተቀበሏቸውን-መልዕክቶች የሚዳስሱ፣ እና እነዚህ ሰዎች - በተማሪዎች የውሳኔ-አሰጣጥ ላይ ምን-ያህል ተፅዕኖ እንዳላቸው ያብራራሉ። በወሲባዊ ውሳኔ-አሰጣጥ ላይ፣ ተጽዕኖ ያላቸውን ሌሎች ምክንያቶችን - ይለያሉ።
2. **ትምህርት/Lesson 2፡ ትክክለኛ የፆታ ትምህርት (accurate sex ed) መረጃን ማግኘት (Finding Accurate Sex Ed Information) –** ትክክለኛ-የሆነ የወሲብ መረጃን የሚያቀርቡ የማህበረሰብ ምንጮችን ለማግኘት፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ (City of Alexandria)ን ድህረ-ገጽን በመመልከት-ይዳስሳሉ። ከአሌክሳንድርያ ውጪ የሚገኙ፣ ትክክለኛ የፆታ ትምህርት (accurate sex ed) መረጃን የሚሰጡ ሌሎች የመረጃ-ምንጮችን መለየት።

**'Standards of Learning':**
10.1, 10.16